# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 201 መጋቢት 13 2004 ገጽ 1


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

የኢትዮጵያ ሙስሊም ማኅበረሰብ ጥያቄ የእምነት ነፃነት ጥያቄ ነው። የኢትዮጵያ ሙስሊም ማኅበረሰብ ጥያቄ የፍትህ ጥያቄ ነው። የኢትዮጵያ ሙስሊም ማኅበረሰብ ጥያቄ የራስን መሪ በራስ የመምረጥ የዲሞክራሲያዊ መብት ጥያቄ ነው። እነዚህጥ ያቄዎች የሁላችንም ጥያቄዎች ናቸው። ስለሆነም ፍትህ፣ ነፃነት፣ እኩልነት፣ ዲሞክራሲ የምትሹ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ከሙስሊሙ ማኅበረሰብ ጎን እንድትቆሙ ግንቦት 7 ጥሪ ያስተላልፋል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የአፍሪካ ቀንድ ሌላ ጦርነት የማስተናገድ አቅም ስለሌለው የወያኔን ጠብ አጫሪነት አለም አቀፉ ህብረተሰብ በጽኑ ሊያወግዝ ይገባል ሲል ግንቦት 7 መግለጫ አወጣ

ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በትናንትናው ዕለትመጋቢት 12 2004 ዓ/ም በእንግሊዘኛ ቋንቋ ባወጣው መግለጫ፤ የኢትዮጵያ ጦር ዓለም አቀፍ ህግን በመጣስ ጎረቤት ኤርትራ ክልል ውስጥ ዘልቆ በመግባት መጋቢት 6 እና ከሁለት ቀን በኋላ ቅዳሜ መጋቢት 8 የሰነዘራቸው ጥቃቶች ክልሉን ወደ ሙሉ ጦርነት የሚከቱ የእብሪት ርምጃዎች ናቸው በማለት ድርጊቱን አውግዞ የሚገርመው ደግሞ የአገዛዙ ባለስልጣናት ይህንን አስመልክቶ በሰጡት መግለጫ ዓለም ዓቀፉን ህግ በመተላለፍ በፈጸሙት ወረራ የኮሩበት መሆኑን በሚያመላክት መንገድ ለዓለም መግለጻቸው እንዳስገረመው ገልጾአል።

ዓለምአቀፉ ማህበረሰብ ለጠብ ፍለጋ ተብሎ በአንዲት ሉዓላዊ ሀገር ላይ የሚደረግን ምክንያት የለሽ ወረራ የሚታገስበት ምክንያት ስለሌለ ለኢትዮጵያው አገዛዝ በግልጽ ሊነግረው ይገባል የሚለው ግንቦት 7 መግለጫ፤ በሁለቱ አገሮች መካከል በ1998 ተካሂዶ የነበረው ጦርነት ምን ያህል አላስፈላጊ መስዋዕትነት እንዳስከፈለና አውዳሚ እንደነበረ ለዓለም አሳይቶአልና እንደገና እንዲደገም ሊፈቀድ አይገባም ሲል አስጠንቅቆአል።

የኢትዮጵያው አገዛዝ ላለፉት ሀያ ዓመታት በውስጥ ከሀገሪቱ ህዝብ ጋር፣ በቅርብ ርቀት ደግሞ ከጎረቤቶቹ ጋር በጦርነት ተጠምዶአል ያለው የግንቦት 7 መግለጫ በህዝባችን ላይ አገር ውስጥ የሚያካሂደው ጦርነት አንሶት በጎሬቤት ኤርትራ ላይ ተመሳሳይ ጥቃቶችን የሚሰነዝረው፤ አገር ውስጥ በአሁኑ ሰዓት የገጠመውን ህዝባዊ ተቃውሞና ለነጻነት፣ ለፍትህና ለዲሞክራሲ የሚነሱ ጥያቄዎችን ለማፈን ነው ብሎአል።

በአንድ ወቅት "የአዲሱ ትውልድ"የአፍሪካ መሪ ሲባል የነበረው መለስ ዜናዊ በሱማሊያ በሚያካሂደው ጦርነት፣ በጋምቤላና በኦጋዴን ባስፈጸማቸው ጅምላ ፍጅቶች ግልጽ የወንጀለኛ ምሳሌ ሆኗል ሲል አብራርቷል።

የአሁኑ ወረራ አለመረጋጋት ባለበት አፍሪካ ቀንድ ከፍተኛ የህዝብ ፍልሰትና ስቃይ ሊያስከትል እንደሚችል ስጋቱን የገለጸው ግንቦት 7 በእርግጥ ኢትዮጵያ ቀጠናውን ለማረጋጋት ወሳኝሚና መጫወት የምትችል ትልቅ ሀገር ብትሆንም፤ እየገዙዋት ባሉት አምባገነኖች ባህሪ ምክንያት እራሷም የችግሩ አካል ሆናለች ብሏል።

በመጨረሻም መግለጫው የተባበሩት መንግስታት፣ ዩናይትድ ስቴትስ፣ የአውሮፓ ህብረት፣ የአፍሪካ ህብረትና ሌሎችም ሰላም ወዳድ ህዝቦች በኢትዮጵያ ያለውን ጦርነት ናፋቂ ስርዓት እንዲያወግዙና በሉዓላዊ ሀገር ላይ የሚደረግ ወረራን መታገስ እንደማይችሉ እንዲነግሩት ጠይቋል።

(ግንቦት 7 ያወጣውን መግለጫ ሙሉ ቃል በገጽ 2 ያንብቡ)

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በጋምቤላ የጸጥታ ማስጠበቁን ስራ ከክልሉ መንግስት ነጥቆ ለመከላከያ እና ለፌደራል ፖሊስ መስጠቱ በምክር ቤቱ ውስጥ ክፍፍል እንደፈጠረ ተዘገበ

የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ኢሳት በትናትና መጋቢት በ10 2004 ዓ/ም ዜና ዘገባው እንደገለጸው፤ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ከፍተኛ የሆነ የጸጥታ መደፍረስ እየገጠማት በመጣው ጋምቤላ ውስጥ ያለው ውጥረት ተባብሶ በመቀጠሉ፤ የክልሉ የጸጥታ ጥበቃ ሥራ በመከላኪያና ፌድራል ፖልሲ ሥር እንዲሆን የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ወስኖአል።

እንደ ኢሳት ዘገባ፤ ባለፈው ሳምንት መጨረሻ አካባቢ ጲጋየ በርሄ፣ የተባለው የመለስ ዜናዊ የጸጥታ አማካሪ ከወያኔ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽነር ወርቅነህ ገበየሁና ሌሎች ከፍተኛ የህወሀት ሹሞች ጋር በመሆን ወደ ክልሉ ተልከው እንደነበርና ለህወሃት ባላቸው ታማኝነትና ታዛዥነት ቀደም ሲል ከወረዳ እስከ ክልሉ ምክር ቤት ከኮለኮሏቸው አመራሮችና የመንግሥት ሰራተኞች ጋር ስብሰባ አድርገው ሲነታረኩና ሲጨቃጨቁ እንደነበር ታውቆአል።

በስብሰባው ላይ ከአዲስ አበባ የተላከው የህወሃት ቡድን በክልሉ እየተፈጠረ ላለው የጸጥታ ችግር ከወረዳ እስከ ክልሉ ምክር ቤት ያሉትን የክልሉን ባለሥልጣናት በመወንጀል ተጠያቂ ሊያደርጋቸው በመሞከሩ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ጥምረት ለነጻነት፤ ለፍትህና ለእኩልነት፤ ከኦሮሞ ነጻነት ግንባር ጋር በፍራንክፈርት ጀርመን የተሳካ ስብሰባ ማካሄዱ ተዘገበ

በጄነራል ከማል ገልቹ የሚመራው የኦሮሞ ነጻነት ግንባር የኦሮሞ ህዝብ መብት ሊከበር የሚችለው በኢትዮጵያ አገራችን ውስጥ የህግ የበላይነትን ሊያከብር የሚችል በህዝብ ውክልና የተመረጠ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት መመስረት ሲቻል ብቻ ነው የሚል አቋም ይዞ ከወጣ በኋላ ላለፈው አንድ ወር ከጥምረት ለነጻነት፤ ለፍትህና ለእኩልነት ጋር በአስራ አንድ የሰሜን አሜሪካ፤ ካናዳና አውሮጳ ከተሞች ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ጋር እያደረገ ያለውን ውይይት በመቀጠል ባለፈው ቅዳሜ መጋቢት 8ቀን 2004 ዓ/ም ፍራንክፈርት ጀርመን ላይ የተሳካ ስብሰባ ማካሄዱን በቦታው የተገኘው ዘጋቢያችን ገለጸ።

በአገሪቱ ሰዓት አቆጣጣር ከቀኑ 9 ሰዓት ተኩል እስከ ምሽቱ አንድ ሰዓት ተኩል በተካሄደው በዚህ ስብሰባ ላይ በጀርመን የተለያዩ ግዛቶች የሚኖሩ በርካታ ኢትዮጵያዊያን መገኘታቸውን የገለጸው ዘጋቢያችን፤ ብዛት ያላቸው የኦሮሞ ማህበረሰብ አባላትና ለመጀመሪያ ጊዜ በርካታ ወጣቶችና ሴት እህቶቻችን የታዩበት እንደሆነ ገልጾአል።

የኦሮሞ ነጻነት ግንባርን በመወከል በስብሰባው ላይ ንግግር ያደረጉት የግንባሩ የውጪ ግንኙነት ሃላፊ የሆኑት አቶ ቃሲም አባነሻ ሲሆኑ ጥምረትን በመወከል የጥምርቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና የአፋር ህዝቦች ፓርቲ የውጪ ግንኙነትና የኢኮኖሚ ሃላፍ ዶር ኮንቴ ሙሳ እንዲሁም የግንቦት 7 ምክትል ሊቀመንበር አቶ አበበ ቦጋለ ናቸው። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በኢትዮጵያ መልካም አስተዳደር ጠፍቷል፤ ቢሮክራሲው በሙስና ተጨማልቆ ነቅዟል፤ ፍትህ ተደርምሷል፤ገንዘብ በህግ ላይ የበላይነቱን አረጋግጧል ሲል አፍቃሪ ወያኔ የሆነው ሪፖርተር ጋዜጣ ገለጸ

መንግሥትም አያውቀውም አይባልም፤ ያውቃል። ቢሮክራሲውም በሌቦች የተሞላ መሆኑን፣ ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነት ህዝቡን ማማረራቸውን፤ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሕዝብ አመኔታ ያጡ መሆናቸውን ያለው ሪፖርተር ተበዳይን ማዳመጥ ለመፍትሄው የጥበብ መጀመሪያ ነው በማለት የወያኔ መንግስት የፍጻሜው መጀመሪያ ላይ መሆኑን በማመላከት ለማንቃት ሞክሯል።

በማያያዝም ንቅዘት በህዳሴ ላይ፣ ብር በፍትህ ላይ የበላይነት ይዟል፤ የፍትህ አካል ተሰነጣጥቆ ተደርምሷል፤ ቢሮክራሲው ተጨማልቋል ብሏል።

ጋዜጣው የሰነዶች ማስረጃ እና የሰው ምስክሮች በሚያስተማምን ሁኔታ በእጁ እያለ ሀቀኛ ባለጉዳይ የሚፈራበት ዘመን ላይ ነን። ፍርድቤቱ በገንዘብ ቢገዛስ ብሎ ባለጉዳዩ ይሰጋል። ወንጀለኞች የበደሉ መሆናቸው እየታወቀ ይስቃሉ። የፈለግነውን ከፍለን የፈለግነውን እናስወስናለን እያሉ ይፎክራሉ። በመጨረሻም ያሸንፋሉ። ገንዘብ ይስቃል፣ ይጮሃል፣ ይዘፍናል፣ ሕግና ፍትሕ ይሸማቀቃል፣ ይሳቀቃል፣ ያለቅሳል:: ይህ በብዛትና በስፋት እየታየ ያለ መከራ ነው ሲል አትቷል።

የህግ አንቀጾች ውበት እንጂ ተግባር መሆን አልቻሉም። በዚህ ብዙ ዜጎች እያለቀሱ ነው። ተስፋ እየቆረጡ ነው። ሀቅ ይዘው የሚደርስላቸው አጥተው እየተሰቃዩ ነው። አቤት የሚሉበት የለም በማለት ያነሳው ዘገባው ወንጀለኛው ሲፈልግ ችሎት ያስቀይራል፤ ሲፈልግ የፖሊስ ምርመራ ያስቆማል፤ ሲፈልግ የታሰረ ያስፈታል፤ ሲፈልግ ንፁሀንን ያሳስራል፤ ሲፈልግ እስረኛ ያስመልጣል፤ ሲፈልግ በቦሌ በኩል ወንጀለኛን ወደ ውጪ ይልካል በዚህም ከመንግሥት በላይ መንግሥት ሆኗል ብሏል።

የህዝብን ብሶት ለማለዘብ ያህል ወንጀለኛ ባለስልጣናት ተገመገሙ ይባላል ይሁንና ሌላ ቦታ ይሾማሉ፤ በተሾሙበት ሆነው እንደገና ይፎክራሉ፤ሀቀኛው ይፈራል፣ወንጀለኛው ያብጣል - እንደ ዘገባው።

ይህነ በተመለከተ የግንቦት 7 ዘጋቢ ያነጋገራቸው አስተያየት ሰጪዎች በበኩላቸው ወያኔ አንድ ዕብሪተኛ፣ ግፈኛና ዘረኛ መንግስት በሚጠላው ህዝብ ላይ ሊፈጽም የሚችለውን በደል ሁሉ እየፈጸመብን ነው ከዚህ በኋላ የምንሰጠው ጊዜ ካለ በቁማችን እንዲቀብረን መፍቀድነው ብለዋል።

እነኚህ ሁሉ ባህሪያት የስርዓቱ መበስበስ ምልክቶች ናቸው ያሉት አስተያየት ሰጪዎቹ በህብረት ገፋ ብናደርገው ይህ ዘረኛ ስርዓት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚወገድበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም በማለት አክለዋል።

## ከሙስሊም ወገኖቻችን ጎን መቆሚያ ወቅት አሁን ነው!!!

ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ያነሷቸው የመብት ጥያቄዎች ምላሽ አላገኙም። የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ እነዚህ የመብት ጥያቄዎች ምላሽ ያገኛሉ ብለን አናምንም። ለመብት ጥያቄዎች የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ የሚሰጠው ምላሽ ጥይት፣ እስርና እንግልት እንደሆነ ሁላችንም ጠንቅቀን እናውቃለን። በዚህም ምክንያት ለመብቶቻቸው መከበር ድምፃቸውን ባሰሙ ሙስሊም ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ላይ ወያኔ የተለመደውን የፈሪ ዱላውን ሊሰነዝር እንደሚችል ምልክቶች እየታዩ ነው። ልክ በምርጫ 97 ማግሥት በቅንጅት መሪዎች ላይ ይደረግ እንደነበረው ሁሉ ዛሬ ከሙስሊም ማኅበረሰብ መሪዎች ላይ የተጠናከረ ስለላ እና የማስፈራራት ዘመቻ እየተፈጸመ ነው። ሙስሊም ወገኖቻችን ግን ትግላቸውን ቀጥለዋል።

ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ እንደገለጽነው በመብት ጉዳዮች ላይ ሁላችንንም ያገባናል። የሙስሊም ዜጎቻችን መብቶች መረገጥ የሁላችንም መብቶች መረገጥ ነው። ለዚህም ነው ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ሃይማኖት ሳንለይ ሁላችንም ከሙስሊም ወገኖቻችን ጎን መቆም አለብን የሚለው።

ወያኔ አንዴ ከክርስቲያኑ ሌላ ጊዜ ደግሞ በሙስሊሙ ጋር የወገነ እየመሰለ ኢትዮጵያዊውን ሙስሊምና ክርስቲያን ለማጣላት ያልፈነቀለው ድንጋይ የለም። በየቦታው በሃይማኖት ሰበብ በሚነሱ ግጭቶች በሙሉ የወያኔ ካድሬዎች እጅ እንዳለበት የአደባባይ ምስጢር ነው። በወያኔ የሃያ ዓመታት ያላሰለሰ የማጋጨት ጥረት ሳቢያ በሁለቱ ትላልቅ ሃይማኖቶችተከታዮች መካከል የነበረው መከባበርና መቻቻል እየሚሸሸ መምጣቱ በሁላችንም ላይ የተደቀነ አደጋ ነው። ይህን አደጋ መከላከል፤ በሃይማኖቶችና በምዕመናን መካከል ያለው መከባበር ቀድሞ ወደነበረት ቦታ መመለስ የዚህ ዘመን ትውልድ ኃላፊነት ነው። ይህንን ለማድረግ ደግሞ አንዱ የሌላው ህመም የራሱም መሆኑን ሊያውቅ ይገባል።

ወያኔ ዛሬ በእስልምና እምነት ላይ እያደረገ ያለው በእብሪት የተሞላ እርምጃ ተመሳሳይ በክርስትና እምነትም ላይ አድርሷል። ያኔ አብረን ባለመቆማችን አሁን የወያኔ እብሪት እስልምና ላይ ዞሯል። ዛሬ ተባብረን ካላስቆምነው ጥቃቱ ተመልሶ ወደክርስትና መምጣቱ አይቀርም። ወያኔ በክርስትና እምነት ላይ ያደረሰውን ውድመት የሚያውቅ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ዛሬ ሙስሊሞች ጎን መቆም ይኖርበታል። ዛሬ በሙስሊሙ ላይ የሚደርሰውን ግፍ በቸልታ የሚመለከቱ ሁሉ የነገ ባለተራ መሆናቸው ሊገነዘቡ ይገባል። በወንበዴዎች በሚገዛ አገር ውስጥ የእምነት ነፃነት እንደማይኖር ከአገራችን የተሻለ ማረጋገጫ አይገኝም።

ስለሆነም በኢትዮጵያ አገራችን ውስጥ እኩልነት እና ፍትህ እንዲኖር የሚፈልግ ሁሉ ዛሬ ከሙስሊም ወንድሞቻችና እህቶቻችን ጎን መቆም ይኖርበታል። በግንቦት 7 እምነት የትግሉም ስትራቴጂያዊ ግብ የመለስን ዜናዊን አምባገነን ሥርዓት በማስወገድ በምትኩ የሃይማኖቶች እኩልነት የሚከበርበት፤ በሃይማኖት ጉዳይ እጁን የማያስገባ መንግሥት መመሥረት መሆን ይኖርበታል።

በ1966ቱ የኢትዮጵያ አብዮት ሙስሊም ማኅበረሰብ የተጫወተው አቢይ ሚና በታሪክ ውስጥ የሚታወሰው ነው። ያኔ ለውጥ ፈላጊ ወጣቶች የሃይማኖት አጥር ሳይከልላቸው በሙስሊሙ ጎን ተሰልፈው ለየካቲት 66 ታላቁ አብዮት መቀጣጠል ትልቅ አስተዋጽዖ አድርገዋል።ታሪክ በ1966 ዓም አዲስ አባባን ያጥለቀለቃት የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ሰልፈኛ በቀኑ ያዜመውን “ክርስትያኖች ወገኖቻችን ተሰለፉ ከጎናችን፤ እንድንሰራ ለሃገራችን” የሚለው ወገናዊ ጥሪ ከትቦ ይዟል። ዛሬም ታሪክ ራስዋን ለመድገም የተዘጋጀት ይመስላል። በወያኔ የማናቆር ፓለቲካ ተጠልፈን ይህንን መልካም እድል አናስመልጥ። የሙስሊም ወንድሞቻችንና እህቶቻንን መነቃቃት ሁላችንንም ያንቃን።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ያነሷቸውን የመብት ጥያቄዎች በሙሉ ልቡ ይደግፋል። ለውጥ ፈላጊ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ደግሞ በሙስሊም ወንድሞቻችንና እህቶቻ ችን ጎን እንዲቆሙ ጥሪ ያደርጋል።

የኢትዮጵያ ሙስሊም ማኅበረሰብ ጥያቄ የእምነት ነፃነት ጥያቄ ነው። የኢትዮጵያ ሙስሊም ማኅበረሰብ ጥያቄ የፍትህ ጥያቄ ነው። የኢትዮጵያ ሙስሊም ማኅበረሰብ ጥያቄ የራስን መሪ በራስ የመምረጥ የዲሞክራሲያዊ መብት ጥያቄ ነው። እነዚህጥ ያቄዎች የሁላችንም ጥያቄዎች ናቸው። ስለሆነም ፍትህ፣ ነፃነት፣ እኩልነት፣ ዲሞክራሲ የምትሹ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ከሙስሊሙ ማኅበረሰብ ጎን እንድትቆሙ ግንቦት 7 ጥሪ ያስተላልፋል። የትግላች ግብ መለስን ማስወገድና በምትኩ ፍትህ፣ ነፃነት፣ እኩልነትና ዲሞክራሲ የሰፈኑባት ኢትዮጵያን መገንባት ይሁን ይላል።

ለዚህ ወሳኝ ትግል ሁላችንም እጅ ለእጅ ተያዘን ለእምነቶቻችና ለራሳችን ስንል በጋራ በመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ላይ እንዝመት።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## የአፍሪካ ቀንድ ሰላምና መረጋጋት እንጂ የጦርነት ከበሮ መስማት አይፈልግም

የግንቦት 7 የፍትህ የነትጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ መግለጫ

መጋቢት 12 2004 ዓ.ም

ባለፈዉ ኃሙስ መጋቢት 7 ቀን 2004 ዓም የወያኔ ሠራዊት በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የሚደረገዉን የሰላም ጥረት በማደናቅፍና የአለም አቀፉን ህግ በመጣስ የኤርትራን ግዛት ወርሮ ማን አለብኝነት የተሞላበት ወታደራዊ ጥፋት ፈጽሟል። ይህ ባለፈዉ ኃሙስ ማለዳ ላይ የተፈጸመዉ የወያኔ ወታደራዊ ትንኮሳና ጥቃት የአፍሪካን ቀንድ ከዚህ ቀደም ታይቶ ወደማይታወቅ ትልቅ የጦርነት እሳት ዉስጥ ሊከትት የሚችል የጀብደኝነት ተግባር ነዉ። የወያኔ አገዛዝ ይህንን የምስራቅ አፍሪካን አካባቢ የጦርነት እሳት ዉስጥ የሚጨምርና የአለምን ሰላም የሚያናጋ አሳፋሪ ወታደራዊ ጥቃት ከፈፀመ በኋላ ይህንኑ አሳፋሪ ድሪጊቱን ለአለም ህዝብ ያሳወቀዉ ትልቅ ገድል እንደፈፀመ ሰዉ በመኩራራት መሆኑ አገዛዙ ምን ያህል በጀብደኝነትና በማን አለብኝነት የተወጠረ እብሪተኛ አገዛዝ መሆኑን በግልጽ ያሳያል።

ኢትዮጵያና ኤርትራ ከ1998 – 2000 ዓም ድረስ ለሁለት አመታት የዘለቀ ጦርነት አካሂደዋል። በዚህ ጦርነት ላይ የጠፋዉ የሰዉ ህይወት፤ የወደመዉ ንብረትና የተፈናቀለዉ ህዝብ ብዛት በእነዚህ ሁለት አገሮች መካከል የሚደረግ ጦርነት ምን ያህል አደገኛ ሊሆን እንደሚችል በግልጽ አሳይቷል። ስለሆነም ግንቦት ሰባት የፍትህ፤የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ አለም አቀፉ ህብረተሰብ የወያኔ አገዛዝ ከጠብ አጫሪነት ተግባሩ እንዲታቀብና ጥቃት ሊፈጸምብኝ ይችላል በሚል መሠረተ ቢስ ፍራቻ ላይ በመመስረት እየተነሳሳ የጎረቤት አገሮችን ድንበር ከመድፈር ተግባሩ አንዲቆጠብ የሚያደርግ እርምጃ እንዲወስድ ይማፀናል።

ባለፉት ሀያ አመታት ወያኔ እመራዋለሁ ከሚለዉ ህዝብ ጋርና ከጎረቤት አገሮች ጋር ጦርነት ዉስጥ መከረሙ በግልጽ የታየ ሀቅ ነዉ። የወያኔ አገዛዝ በየአቅጣጫዉ የሚያካሄደዉ ጦርነት ከአገር ጥቅምና ደህንነት ጋር የተያያዘ አይደለም። ይልቁንም ወያኔ የጦርነት ከበሮ መምታት የሚጀምረዉ አገር ዉስጥ ከህዝብ የሚመጣዉን የነፃነት፤ የፍትህና የዲሞክራሲ ጥያቄ አቅጣጫ ለማስቀየርና የስልጣን ዘመኑን ለማራዘም ብቻ መሆኑን በተደጋጋሚ የወሰዳቸዉ ፀረ ህዝብ እርምጃዎች በግልጽ አሳይተዋል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሶማሊያ ዉስጥ የሚያካሄደዉ የዉክልና ጦርነትና ጋምቤላና አጋዴን ዉስጥ የሚያካሄደዉ የዘር ማጥፋት ወንጀል ይህ አንድ ሰሞን ችኩሎች የአፍሪካ ተስፋ ነዉ ያሉት ሰዉ ምን ያክል የአፍሪካን ተስፋ የሚያጨልም አደገኛ ሰዉ ለመሆኑ ማስረጃ ነዉ። ሰላም ወዳዱ የኢትዮጵያ ህዝብና ግንቦት 7 የወያኔ አገዛዝ ለኢትዮጵያ ሰላምና ደህንነት አንዲሁም ለምሰራቅ አፍሪካም ሆነ ለአለም ሰላም የማይበጅ አደገኛ አገዛዝ መሆኑን በሚገባ ይረዳሉ። በዚህ አጋጣሚ ግንቦት 7 የወያኔ አገዛዝ በቅርቡ ኤርትራ ላይ የወሰደዉ የጠብ አጫሪነት እርምጃ በምስራቅ አፍሪካ አካባቢ ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ የህዝብ እልቂትና መፈናቀል ሊያስከትል የሚችል አደገኛ አዝማሚያ መሆኑን የአለም አቀፍ ህብረተሰብ እንዲገነዘብና አስፈላጊዉን ጥንቃቄ አንዲያደርግ ከወዲሁ ማስጠንቀቅ ይፈልጋል።

ኢትዮጵያ ካላት የህዝብ ብዛት፤ የቆዳ ስፋትና ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ አኳያ የምስራቅ አፋሪካን አካባቢ ሰላምና መረጋጋት በማስከበሩ ረገድ ከፍተኛ ሚና መጫወት መቻሏ የሚያጠራጥር አይደለም፤ ሆኖም ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉ አገዛዝ በዘረኝነትና በጠብ አጫሪነት ላይ የተመሰረተ አስከሆነ ድረስ ኢትዮጵያ የአካባቢዉ ሰለምና መረጋጋት መደፍረስ ዋነኛ ምክንያት መሆን እንደምትችልም መገንዘብ ያስፈልጋል። ስለሆነም ግንቦት 7 የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን፤ የአዉሮፓ ህብረትን፤ የአፍሪካ ህብረትንና ሰላም ወዳዱን የአለም ህብረተሰብ የወያኔን ጠብ አጫሪነት አንዲያወግዙና አለም አቀፉ ህብረተሰብ እብሪተኝነትንና የአገሮችን ሉዓላዊነት የሚጥስ ወረራ በትዕግስት ዝም ብሎ እንደማይመለከት በግልጽ ማሳወቅ እንዳለበት ያሳስባል።

## ጥምረት ለነጻነት፤ ለፍትህና ለእኩልነት፤ ከኦሮሞ ነጻነት ግንባር ጋር በፍራንክፈርት ጀርመን . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

በተለያዩ ጊዜያቶች ሥልጣን ላይ የተፈራረቁ የኢትዮጵያ አገዛዞች በኦሮሞ ህዝብ ላይ የፈጸሙትን የመብት ረገጣ ለማስቆምና የኦሮሞን ህዝብ ነጻ ለማውጣት ኦነግ ላለፉት 40 አመታት ያካሄዳቸውን ትግሎችና በሂዴት የተመዘገቡ ድሎችን ጠቅለል አድርገው ለስብሰባው የገለጹት የግንባሩ ተወካይ አቶ ቃሲም አባነሻ፤ ድርጅታቸው ኦነግ የፕሮግራም ለውጥ ለማድረግ የቻለው የኦሮሞ ህዝብ ነጻ ሊወጣ የሚችለው አናሳ የሆነው የወያኔ አገዛዝ በሁሉም ህዝባችን ላይ እያደረሰ ያለውን ኢፍትሃዊነት በጋራ ትግል ማስቆምና ወያኔን ማስወገድ ሲቻል ብቻ እንደሆነ በማመኑ እንደሆነ ገልጸው፤ ፍትህ፤ እኩልነትና ነጻነት የሰፈነባት ዲሞክራሲዊት ኢትዮጵያን ከሌሎች ዲሞክራቲክ ሃይሎች ጋር ሆኖ ለመመስረት ቁርጠኝነት እንዳላቸው አስታውቅዋል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

---

## የእሳት እራት

### ትውስታየ በውጭ ጉዳይ ሚንስቴር (ክፍል 5 ካለፈው ሳምንት የቀጠለ የመጨረሻ ክፍል)

ዘሪሁን ረታም ህወሃቶች ከገቡ በኋላ የመጣ ነው። ዘሪሁን ረታ አጭርና ብልጣ ብልጥ ነው። በመስሪያ ቤቱ ሠራተኞች ዘንድ ቀራጩ ዘኬዎስ ተብሎም ይጠራል። ቤተክርስትያን አካባቢም አይጠፋም። ዘሪሁን ረታ የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት ኃላፊ ሁኖ ሲሰራ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ላይ ባላ አንድ ፎቅ ቤት ሰርቶ ቢጨርስም ካዛእንቺስ አካባቢ የመንግስት ቤት ውስጥ ይኖራል። ላፍቶ ላይ ያሰራውን ቤት ያዩ ሰዎች በጣም ተገርመው የገንዘቡን ምንጭ ቢፈልጉ ቢፈልጉ ሊያገኙ አልቻሉም። የዘሪሁን ደሞዝ ቢበዛ ሶስት ሺህ የኢትዮጵያ ብር ነው። ሙሉ ደመወዙን ሳይበላ ሳይጠጣ ለመቶ ዓመት ቢያጠራቅም እንኳ እንዲያ ያለ ቤት ሊሰራ አይችልም። ታዲያ ጥያቄው ያን ሁሉ ብር ከየት አምጥቶ ነው ያን "ground plus " ህንጻ ሊሰራ የቻለው ? ዘሪሁን ረታ ዘው ብሎ የገባበት የሙስና አዘቅት መኖሩን ላፍቶ ከተማ ላይ ጉብ ያለው ቤቱ ይመሰክርበታል። ከዚያ አዘቅት ውስጥ መቼም ቢሆን የሚወጣ አይደለም። እዚያው ሆኖ ሲጠሩት አቤት ሲልኩት ወዴት እያለ ከመኖር ውጪ ሌላ አማራጭ ያለው አይመስልም። ከዚያም በዚያች በምናምን በሞላት ቦርጩ ላይ ያንጠለጠላትን ካራባት እየነካካ እንደ አደይ አበባ ፈክቶና አምሮ ደግ ዘመን እንዲመጣ እየጸለየ ይኖራል እንጂ ሌላ አይናገርም። ለነገሩ ህንጻ ሠርቶ የማከራየት ነገር ከተነሳ "አምባሳደሮችን" ለምሳሌ ተሾመ ቶጋን፤ገነት ዘውዴን፤ አዲስዓለም ባሌማን ጠቅሰን እነዚህ ግለሰቦች ከየት አምጥተው ቦሌ ላይ ህንጻ ሊሰሩ ቻሉ ብለን ብንጠይቅ መልስ የሚሰጠን ይኖር ይሆን ?

በእነዚህ ሰዎች አስፈጻሚነት 42 ሰራቶች ተባረርን። መለስ ተ/ማሪያምም ሞተ። አቶ አክሎግ እምሩም ሞተ።

መለሰ ተ/ማሪያም ቅንና ትሁት ሰው ነበር። የሰው ልጆችን በምንም ሁኔታ ለማስቀየምም ሆነ ለመጉዳት የማይፈልግ በጥንቃቄ ለመኖር ጽኑ እምነት የነበረው ሰው ነበር። ይሄ ጽኑ እምነቱ ነው ማንንም ሳይጎዳ ማንንም ሳይጠቅም ታንቆ እንዲሞት ያደረገው። ብዙዎቻ መሞቱ ካልቀረ ለምን ለዚያ ደረጃ ካደረሱት ሰዎች መካከል አንዱን ገድሎ አይሞትም ብለው እንደተናደዱበት አውቃለሁ። መለሰ ተ/ማሪያም ግን ማንንም በምንም ሁኔታ ለመጉዳት ፍላጎት አልነበረውም። ይሄ የእርሱ እምነት ነው። በዚህ መሠረት ለዚህ ያበቁትን ሰዎች ለሂሊና ፍርድ ትቷቸው ዳግም ላይመለስ ሂዷል።

ሰዩም መስፍን እንኳ ደም በማፈሰሰ ከኖረ ድርጅት ውስጥ የወጣና ደም ማፈሰስ ልማዱ ስለሆነ ሂሊናው ይወቅሰዋል ብለን አንጠብቅም። ስዩም ማታ የተኛትን ሴት ቀን በመርዝ ለመግደል ወደ ኋላ እንደማይል ከቀድሞ ጓዱ ሰምተን ተገርመናል። ከእርሱ ምንም በጎ ነገር አይጠበቅም።

ተቀዳ ዓለሙ፤ ዘሪሁን ረታ እና ሌሎች ግን ስሙ !!! ዓይኖቻችን በእናንተ ላይ ናቸው !!! "አማራ የትግራይ ህዝብ ቀንደኛ ጠላት ነው" ብሎ ከሚያስብ ሃይል ጋር ነው አብራችሁ የተሰለፋችሁት። እናንተ አማሮች ናችሁ። እናንተም አይደለንም አላላችሁም። ግን ምን ዓይነት አማሮች ትሆኑ !? በእርግጠኝነት እነስዩም መስፍን "አህያ" እያሉ የሚሳድቧችሁ እንደእናንተ ዓይነቱን ነው። ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋን "አህያ" እንደማይሉ እኔ እነግራችኋለሁ። ፍትህን አጉድሎ፤ነጻነቴን ገፎ እና አማራን እንደጠላት ቆጥሮ በዚህ አገር ላይ ከሰለጠነ ኃይል ጋር አብሬ ከምኖር ብሎ ራሱን በእሳት ያጋየውን መምህር የኔሰው ገብሬን የሚያከብሩትን ያህል ለእናንት ቅንጣት ታክል ክብር እንደሌላቸው እኔ እንግራችኋለሁ። እናንተን አቶ ሃዱሽ ሳይቀር ይንቋችኋል። ምክንያቱም እነርሱ የሚያምኑበትን ሲያደርጉ እናንተ ልታምኑ የማይገባችሁን አለቦታችሁ አለሰገባችሁ ተገኝታችሁ ለምትበሉትና ለምትጠጡት ስትሉ አንገታችሁን ደፍታችሁ መኖርን መርጣችኋል። ስለዚህ በእነርሱ ዘንድ ትናቃላችሁ በሌላው ዘንድ ደግሞ ትወገዛላችሁ።

እኔና ሌሎች አርባ አንድ ሠራተኞች ተባረን ጦም ማደር የጀመርነው እናንተ ዓይናችሁ እያየ ነው። መለስ ተ/ማሪያምም ተስፋ ቆርጦ ራሱን አንቆ የገደለውም በእናንተ ዓይነት አሳሞች ምክንያት ነው።

በነገራችን ላይ ከተባረሩት መካከል የሞተው መለሠ ተ/ማሪያም ብቻ አይደለም። አቶ አክሎግ እምሩም ሙቷል። የአማሟቱ ሁኔታ ግልጽ አይደለም። እንደተሰማው ከሆነ ተከራይቶ የሚኖርበት ቤት ውስጥ ሞቶ ተገኝቷል። አቶ አክሎግ እምሩ በውጭ ጉዳይ ሚንስትር ከአስር ዓመት በላይ አገልግሏል። አቶ አክሎግ እምሩ ከአስር ዓመት በላይ በውጭ ጉዳይ የሠራ ቢሆንም ከትምህርቱና ከሥራ ልምዱ ጋር የሚመጥን የሥራ ደረጃ ላይ አልነበረም። ምክንያቱ ደግሞ ከእለታት አንድ ቀን ሸራተን ይሁን ሂልተን ሆቴል ውስጥ ተደርጎ በነበረው ግብር ላይ አቶ አክሎግ ገስግሶ ሂዶ ስዩም መስፍንን "እኔን መቸ ነው የሚመድቡኝ ሲል ይጠይቀዋል" ሰዩምም እንዴት ደፍሮ እንዲህ ይጠይቀኛል ብሎ ቂም ቋጠረበት። ከዚያች ጥያቄ በኋላ አቶ አክሎግ እምሩ ከደረጃው ዝቅ ብሎ ወደ ማይመጥነው ቦታ ተመድቦ እንዲሰራ ተደረገ። ቅንጅት ሲመጣ ምክንያት ተገኘና ከተባራሪዎቹ አንዱ ሆኖ አረፈው። ከተባረረም በኋላ ብዙም ሳይቆይ ሞቶ ተገኘ ተብሎ ሰማን። በውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ውስጥ ብዙ ሠራተኞች በድንገት ሞተዋል። ለምሳሌ ደሳለኝ ዓለሙ የዓለም አቀፍ ዳይሬክቶሬት ተ/ዋና ዳይሬክተር ሆኖ በመስራት ላይ እያለ መታመሙ ሳይሰማ ሞተ መባሉን ሰምተናል። አምሳሉ መለስም እንዲሁ በድንገት ሙቶ ተገኝቶቷል።

አሁን አሁን የገባኝ የህወሃት እና የሌሎች ኢትዮጵያዊያን ልዩነት የጭካኔና የሂሊና ጥያቄ ጉዳይ ነው። እነርሱ የጭካኔያቸው መጠን ልክ ሲያጣ እኛ የሚጨክን ልብ ማጣታችን። እኛ የሂሊናና የሞራል ጥያቄ ወጥሮ ይዞን ሰውስ እግዜርስ ምን ይለናል የምንል ሲሆን እነርሱ ከእነዚህ ነገሮች ጋር ፈጽሞ አለመተዋወቃቸው ነው።

እናም 42 ሠራተኞችን ለቃቅመው አባረሩ። እኔም የአገሪቷን አመራሮች ብቃት ትጠራጠራለህ ተብየ እንድባረረ ተፈረደብኝ። አንድ ጓደኛየም የተባረረበት ምክንያት ጠቅላይ ሚንስትሩን ሰድበሃል ተብሎ ነው። ምን ብሎ እንደተሳደበ ሲጠየቅ አንድ ቀን ተናድጄ ይሄ "ክፉ መላጣ"ብየዋለሁ ብሏል። ሌላውም የተባረረውም ከጓደኞችህ ጋር ስታወራ የኢትዮጵያ ፌዴራል ሥርዓት "immature" ነው ብለሃል ተብሎ ነው።

ከዚህ በኋላ ልቤ ቂም እንደቋጠረ ተነሳሁና ወደ ወላጆቼ ክፍለ ሃገር ሄድኩ። ሁላችንም ተያይዘን ሃዘን ተቀመጥን። ምኞታችን ሲሞት፤ ተስፋችን ሲጨልም በራሳችን ላይ ትቢያ ነስንሰን ማቅም ለብሰን ሃዘን ብንቀመጥ የሚፈርድብን ይኖር ይሆን ?

ልጄ አንተንም አባረርሁ ሲል ተክዞ ጠየቀኝ አባቴ።

አዎን እኔንም አባረሩኝ።

አየህ እነዚህ ሰዎች እንዲመጡ ትንቢት ተነግሯል። እንደመጡም የሚሄዱበት ግዜም እንደሚመጣ ተነግሯል። ጉንዳኖች ናቸው። ጉንዳን ሲገባ ጻጥ ብሎ ይገባል የሚፈጅውንም ፈጅቶ በየት በኩል እንደሄደ ሳይታወቅ ይጠፋል።

ይህን ትንቢት ማን እንደተናገረው የሚታወቅ ነገር የለም። በአገራችን እንዲህ ያሉ ምንጫቸው ያልታወቁ ብዙ የታመኑ ትንቢቶች አሉ።

ልጄ አንተ በእግዚአብሄር ታምናለህ አለኝ አባቴ። አዎን በእግዚአብሄር እንድታምን ሆነህ ነው ያደከው። አንተ ከእነዚህ ሰዎች የምትለየው በዚህ ነው። አንተ በእግዚአብሄር ታምናለህ እነርሱ ግን አግዚአብሄር ከላይ ሁኖ ሁሉን እንደሚያይ ነገም እንደሚፈርድባቸው አይረዱትም። አንተ ከእነርሱ ከፍ ትላለህ። አዎን እነርሱ ከሰው ልጅነት ስብእና የወረዱ እንደ አራዊት ኑረው እንደአራዊት የሚሞቱ ናቸው። ልጄ ሌላ ክፍ ነገር እንዳታስብ።

እናቴ እንደተከዘች ከበርጩማዋ ቁጭ እንዳለች ደጅ ደጁን ትመለከታለች እንጂ አስተያየት አትሰጥም። ህወሃቶች አባት፤እናትንና ልጅን ባንድነት ያስለቅሳሉ ያሳዝናሉ። ከተባረርነው መካከልም አግብተው ልጅ ያላቸው የሚጦሯቸው አባትና እናትም ያላቸው አሉ። ህወሃቶች የሚያስለቅሱት ሁለት ትውልድን ብቻ ሳይሆን አያት፤ አባትና የልጅ ልጅን ነው። ፕሮፌሰር መስፍን በአንድ ወቅት ሦስት ትውልድ በአንድነት ያለቀሰበት ዘመን ብለው መናገራቸው ይሄው በውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ሠራተኞች ተገልጧል።

ይህችን ጦማር ስጽፍ አባቴ ዳግም ወደማይመለስበት ዓለም ሂዷል። የትንቢቱንም ፍጻሜ አላየም። እኔ የትንቢቱን ፍጻሜ አያለሁ ብየ ተስፋ እያደረኩ ነው። እንደ ጉንዳን እንደገቡ እንደ ጉም ብን ብለው እነደሚጠፉ እያሰብኩ በተሰፋ እየኖርኩ ነው። ተስፋየም እውነት እንዲሆን የምችለውን አደርጋለሁ።

እግዚአብሄር ከላይ ከሰማይ ሁኖ እንባችንና ሃዘናችንን ይመለከታል። ዝም አይልም። እኔም ዝም አልልም። ለሞት የሚያደርስኝ እንኳ ቢሆን እነዚህን ምናምንቴ ቡድኖች ግዜው ሲደርስ ከመፋለም ወደ ኋላ አልልም። አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ እግዜር ባኖረኝ መንገድ እየኖርኩ ነው። ስሜን አልናገርም። ለምን ብየ ጠላቶቼ የት እንዳለሁና ምን እንደምሰራ ይወቁ። የብእር ስሜን እነሆኝ። ነጻነት ለሁላችን ይሁን ነኝ።

ቸር እንሰንብት!!

ነጻነት ለሁላችን ይሁን ነኝ።

## ጥምረት ለነጻነት፤ ለፍትህና ለእኩልነት፤ ከኦሮሞ ነጻነት ግንባር ጋር በፍራንክፈርት ጀርመን . . . (ከገፅ 3 የዞረ)

የጥምረት ተወካይ የሆኑት ዶር ኮኒቴ ሙሳ በበኩላቸው፤ ወያኔ ለከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲው እንዲመቸው ሲል በህዝባችን መካከል በዘራው ፕሮፖጋንዳ እርስ በርስ መፈራራትና መጠራጠር ስለሰፈነ መተማመን አስቸጋሪ እየሆነ መምጣቱን ገልጸው፤ አገራችንን ነጻ ለማውጣትና ህዝባችንን ከጭቆና ለማላቀቅ ከተፈለገ ወያኔና ቀደምቶቹ አገዛዞች ሆን ብለው የፈጠሩብንን የርስ በርስ ጥርጣሬ አስወግደን በመተማመን አብረን መታገል ይኖርብናል ብለዋል። ዶር ኮንቴ አለመተማመን በስነልቦናችን ላይ ሊፈጥር የሚችለውን ተጽዕኖ በሳይንሳዊ ትንታኔ በማቅረብ ቤቱ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኝ አድርገዋል።

..............................................................................................................................................

## የወያኔ ባለሥልጣናት የሙስና ቅሌት መጋለጡ ቀጥሎአል። የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት ሃላፊ እሌኒ ገብረመድህን እንዲ መሆኗ ተዘገበ

ሰሞኑን አንድ ከአለም ባንክ የተገኘ መረጃ ይፋ እንዳደረገው አለም ባንክ ለኢትዮጵያ ሊሰጥ የነበረው 5 ሚሊዮን አካባቢ የአሜሪካን ዶላር የኢትዮጵያ ምርት ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ሆና በመለስ ዜናዊ በተሾመቺው እሌኒ ገብረመድህን ሊመዘበር እንደሆነ መረጃ በማግኘቱ እርዳታውን መሰረዙን ለማወቅ ተችሎአል።

የአለም ባንክ ለኢትዮጵያ ከሚሰጠው ገንዘብ ውስጥ 4 ሚሊዮን 8 መቶ ሽ የአሜሪካን ዶላር የምርት ገቢያ ድርጅትን አቅም ለመገንባት በሚል ሰበብ ለእሌኒ ገብረመድህን እንዲሰጥ የጠየቀው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ቀደም ሲል በድርጅቱ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የሃብት ዘረፋና ሙስና እንደሚካሄድ እያወቀ ምንም እርምጃ ሳይወስድ ይህንን የሚያክል ገንዘብ እንዲሰጥ መጠየቁ የዘረፋው ተባባሪ መሆኑን ያመለክታል ተብሎአል።

እንደመረጃ ምንጩ የአለም ባንክ ለእርዳታ ሊሰጥ የነበረውን ይህንን ገንዘብ ሊሰርዝ የቻለው የምርት ገቢያ ድርጅትን አቅም ለመገንባት በሚል ሰበብ ኢሌኒ ገብረመድህን ያለምንም ተወዳዳሪ ሚሊኒየም አይቲ ከተባለ በሰሪላንካ ከሚኖር አንድ ድርጅት ጋር በመመሳጠር ጫረታ አሸንፎአል በሚል የሃሰት ቅንብር የስራ ተቋራጭነት ኮንትራት ለመፈራረም ሽር ጉድ ላይ መሆኗን መረጃ ካገኘ በኋላ እንደሆነ ታውቆአል።

የአለም ባንክ አግኝቶታል በተባለው መረጃ ሚሊኒየም አይቲ የግንባታ ሥራውን ለማከናወን የጠየቀው ገንዘብ 3 ሚሊዮን 5 መቶ ሺ የአሜሪካን ዶላር ሆኖ እያለ በነ እሌኒ ገብረመድህን ተቀናብሮ ለአለም ባንክ የቀረበው ሰንድ ግን የሚያመለክተው ድርጅቱ 4 ሚሊዮን 855 ሺ ዶላር እንደጠየቀና ጫረታውንም እንዳሸነፈ የሚያሳይ ነበር። በዚህ መሰረት የህወሃቷ ምርጥ ልጅ ወ/ሮ እሌኒ ከ 1 ሚሊዮን 270 ሺ የአሜሪካን ዶላር ወይም ከ20 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር ያላነሰ ገንዘብ በአንዴ ለማግኘት ስታሰፍስፍ የአለም ባንክ ባለስልጣናት እጅ ከፍንጅ ይዘው ጉሮሮዋን ዘግተአል።

ለውጪ ገቢያ ሊላክ የተዘጋጀ አንድ መቶ ቶን በላይ የተጣራ ቡና የደረሰበት ያልታወቀው እሌኒ ገብረመድህን በሃላፊነት በምትመራው የምርት ገቢያ ድርጅት ውስጥ መሆኑን ጨምሮ ድርጅቱ ውስጥ ከፍተኛ ሙስና እንደሚካሄድበት ቀደም ብሎም ቢሆን እንደሚታወቅ የሚናገሩት ምንጮች፤ ሙስናን እዋጋለሁ የሚለው የጸረ ሙስና ኮሚሽን ጉዳዩን እያወቀ ምንም እርምጃ ለመውሰድ አለመድፈሩ የመለስ ዜናዊና የባለቤቱ አዜብ መስፍን እጅ ያለበት መሆኑን ያሳያል ብለዋል።

## የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ባለስልጣናት እያየለ የመጣው የኑሮ ውድነት ከቁጥጥር ውጪ እየሆነ መምጣቱን ለመናገር ተገደዱ

የወያኔ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር የሆነዉ ሱፍያን አህመድ የመሥሪያ ቤቱን የስድስት ወራት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለወያኔዉ ተወካዮች ምክር ቤት ሲያቀርብ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ የተከሰተው የዋጋ ግሽበት፤ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፤ በመንግሥትና ባጠቃላይ በአገር ደረጃ ፈታኝ ችግር መሆኑን ተናገረ፡፡

በማያያዝም የዋጋ ግሽበቱን ተከትሎ ለማረጋጋት የወሰዱትም እርምጃ የዋጋ ንረት የታየባቸውን መሠረታዊ ፍጆታዎች ማለትም (ስንዴ፤ ስኳርና ዘይት) ከውጭ በማስመጣት በድጐማ ለኅብረተሰቡ ማቅረብ እንደነበር ያስታወሰዉ ሱፊያን ሆኖም የማረጋጋት እርምጃዉ በተለዩ ምክንያቶች ለውጥ ሊያመጣ አለመቻሉን ተናግሯል።

ከሁሉም በላይ በዋጋ ግሽበቱ የሚጐዳው ዝቅተኛው የኅብረተሰብ ክፍል መሆኑን የገለጸዉ ሶፊያን በማያያዝም ችግሩ በአገር ደረጃ የሚካሄደውን ድህነትን የመዋጋት እንቅስቃሴ የሚፈታተን ሆኗል በማለት ወያኔ እስከዛሬ ድረስ ሲሸፋፍነው የኖረውን ችግርና የሁለት አሃዝ እድገት ባዶነትን አጋልጦአል።

የአገራችን ገበሬ በምርታማነቱ ብዛት ሚሊዮነር ሆኖአል በማለት በህዝባችን ችግር ሲያላግጥ የኖረው የህወሃት ቡድን አገሪቱን በገጠማት መሰረታዊ የፍጆታ ምርቶች እጥረት ምክንያት ስንዴ፣ ዘይትና ስኳር የመሳሰሉትን ከውጪ አገር በማስመጣት ለማከፋፈል ለረጅም ጊዜ የተደረገው ጥረት ችግሩን ለመቅረፍ እንዳላስቻለና ይልቁንም እየተባባሰ እንደሄደ አልደበቀም።

በአገር ውስጥ እየተባባሰ የመጣው የኑሮ ውድነት በቶሎ መፍትሄ ካላገኘ ለአገዛዙ ሕልውና እንደሚያሰጋ እየወተወተ ያለው አፍቃሪ ወያኔ የሆነ ጋዜጣ ሪፖርተር በበኩሉ 'የኑሮ ዉድነት የጭነቱ ልክ ስንት ነዉ" በሚል ርዕስ ባወጣዉ ዘገባዉ ለጠላትም መግቢያ ቀዳዳ ይከፍታልና ኋላ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ ያስፍልጋል በማለት ህወሃት አለቆቹን አስጠንቅቆአል።

የአንድ ኩንታል ጤፍ ዋጋ አዲስ አበባ ላይ አንድ ሺ ሰባት መቶ ብር መድረሱ አጅግ አስደንጋጭ ነው የሚለው ሪፖርተር እየናረ የመጣው የጤፍ ዋጋ ብቻውን ከአብዛኛው የመንግሥት ሰራተኛ አማካይ የወር ደመወዝ በልጦአል፡፡

በዚህ ላይ የቤትኪራይ፣ የትራንስፖርት፣ የልብስ፣ የምግብ፣ የልጆችማስተማሪያ፣ የመድኃኒት ወጪ፣ ወዘተ ሲጨመርበት ገቢና ወጪ "አራምባና ቆቦ" እየሆኑ ናቸው ፡፡ ገቢ "እፍኝ" ወጪ "ክምር" እየሆነ አልጣጣም ብሏል፡፡ በማለት ህዝቡ ያለበትን ብሶት ሪፖርተር ገልጾአል።

ኑሮ እየከበደ መምጣቱን ሁላችንም የምንስማማበት ችግር እየሆነ መጥቶአል የሚለው ሪፖርተር ኅብረተሰቡ የኑሮ ውድነቱን እስከ መቼ ይሸከመዋል የሚለው ዓቢይ ጥያቄ ሆኖአል ካለ በኋላ የኑሮ ውድነቱ የጭነት ልክ ስንት እንደሆነ ጠይቆአል።

ይህ በዚህ እንዳለ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ መምህራን የኑሮ ውድነቱ በፈጠረባቸው ጫና ተማረውና ሰሞኑን ወያኔ አደረኩ ያለውን የይስሙላ ደመወዝ ጭማሪ በመቃወም የሥራ ማቆም አድማ ሊጠሩ በምክክር ላይ እንደሆኑ የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ኢሳት ዘግቦአል።

የኑሮ ውድነቱና የሙብት አፈናው ህዝባችንን እጅግ እያሰቃየ ባለበት በአሁኑ ሰዓት ወያኔ የህዝብ ትኩረት ወደጦርነት ለመውሰድ ጎሬቤት ኤርትራን የመተናኮልና ጦርነት የመቀስቀስ ድርጊቱን እንደገፋበት በየቀኑ እየተሰጠ ያለው መግለጫ ያመለክታል።

በየአመቱ እስከ 14 ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝባችን በአለም አቀፍ የምግብ እርዳታ ውስጥ እየኖረ ወያኔ የአገሪቱን ሃብት ትርጉም ለሌው ጦርነት ለማዋል የሚያደርገው ጥረት በጦርነትና በወከባ ብዛት የስልጣን ዕድሜውን የሚያረዝም መስሎት እንደሆነ ታዛቢዎች ይናገራሉ።

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በጋምቤላ የጸጥታ ማስጠበቁን ስራ . . .

(ከገፅ 1 የዞረ)

በተፈጠረው አለመግባባት ምክር ቤቱ ለሁለት መከፈሉን የገለጸው ኢሳት፤ ጴጋየ በርሄና ፕሬዚዳንቱ አመድ አባንግ በመሩት ስብሰባ ላይ የተነሱት ዋና ዋና ነጥቦች በክልሉ ፕሬዚዳንት የስልጣን እድሜና በክልሉና በፌደራል መንግስቱ መካከል እየተበላሸ ስለመጣው ግንኙነት ነበር ብሎአል።

አንድ የክልሉ ከፍተኛ ባለስልጣን ለፕሬዚዳንቱ አባንግ ኦማት "ለአንተ የተሰጠው የስልጣን ጊዜ 6 ወር ነበር፣ አሁን ያ ቀን ከመድረሱ በፊት ስልጣንክን መልቀቅ አለብህ። በአንተ ምክንያት ነው ህዝብ እያለቀብንና እየተፋጀ ያለው። ለአንተ ሲባል የእኛ ልጆች መጨረስ የለባቸውም።" ማለቱን የዘገበው ኢሳት ሌላ ስሙ ያልተገለጸ ባለስልጣን ደግሞ "አንተ ከፌደራል መንግስት ጋር በመመሳጠር መሬታችንን ያለእኛ እውቅና ሸጠሀል። መሬቱ የሚቸበቸበው እኛ አኝዋኮች በማናውቀው መንገድ ነው። አንደኛው የችግር ምንጭም ይህ ነው" ማለቱን ዘግቦአል።

ከማዕከል በመጡት የህወሃት አለቆቻቸው ፊት እርስ በርስ ሲወነጃጀሉ የነበሩ የክልሉ ባለስልጣናት ከብስጭት ብዛት ለሁለት ተከፍለው ገሚሶቹ ከአሁን በኋላ "በህገ መንግስቱ አንመራም፣ ራሳችንን ችለን ማስተዳደር ነው የምንፈልገው፣ ከፌደራል መንግስት ተብዬዉም ምንም አይነት ድጎማ አንፈልግም፤ ጁባ ራሷን ችላ እንደምትተዳደረው እኛም የፌደራል ጥገኛ ሳንሆን ራሳችንን ችለን እንተዳደራለን። የፌደራል መንግስት ጥገኞች በመሆናችን የተረፈን መሬታችንን በህገ ወጥ መንገድ መቸብቸብ ነው። "የሚል አቋም እስከማራመድ እንደደረሱና ከፉኛ ሲጠዛጠዙ እንደነበር ኢሳት ምንጮቹን ገልጾ ዘግቦአል።

በክልሉ ባለስልጣናት አቋም የተደናገጡት የህወሃት መልዕክተኞች፣ እንዲህ አይነት አቋም የሚያራምዱ ባለስልጣናት ምናልባት ጸጥታ በማወክ በኩል እጃቸው ሳይኖርበት አይቀርም በሚል ጉዳዩ እንዲጣራ ወስነዋል ያሉት የኢሳት ምንጮች የክልሉ መስተዳድር የጸጥታ ሁኔታውን ለመቆጣጠር ከአቅሙ በላይ በመሆኑ፣ ከአሁን ቦኋላ መከላከያና ፌደራል ፖሊስ ሃላፊነቱን እንደሚወስደው ገልጧል ብሎአል።

በክልሉ የተላከው የህወሃት ቡድን ጴጋዬ በርሄና ወርቅነህ ገበየሁ ከክልሉ ፕሬዝዳንት ኦማት አመድ ጋር በመሆን በቅርቡ ወደ ጋምቤላ ሲጓዙ የተገደሉትን የሚች ቤተሰቦች ለመጎብኘት ጎደሬ ከተባለው ስፍራ ሲደርሱ የነርሱን ወደስፍረዉ መምጣት ያወቁ ነዋሪዎች የጋምቤላ ክልል ባንዲራ አወርደው ሲያቃጥሉ መድረሳቸው ተዘግቦአል።

ህወሃት የጋምቤላን ድንግል መሬት ነዋሪዎቹን በማፈናቀል ካራቱሪ ለሚባል የህንድ ካምፓኒና ለሼክ አላሙዲ ማከፋፈሉ የቀሰቀሰው ህዝባዊ ተቃውሞ ለወያኔ ከፍተኛ ራስ ምታት እንደሆነበት በተደጋጋሚ መዘገቡ አይዘነጋም።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ፦** በ 358 MB, በ 837 kHz

**አጭር ሞገድ፦** በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታሳውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ፦ ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org